‹ **ታማኝነት**

ታማኝነት ማላት በቃል መገኘት፤የተቀበሉትን አደራና ኃለፊነት በአግባቡ መወጣት፤እውነተኛ መሆን ማለት ነው፡፡

ተማኝነት በእግዚአብሔር ባሕርይ ያለች የባሕርይ ገንዘቡናት፡፡ እግዚአብሔር በቃሉ፤በሥራው በተስፋው ታማኝ ነው፡፡እንደ ቃሉ ይሠራል፤ለሥራው ጉድለት ወይም አድልዎ የለበትም፡፡በሰጠው የተስፋ ቃል አይጠረጠርም፡፡ ” እግዚአብሔር በቃሉ የታመነ ነው በሥራ ሁሉ ጻድቀ ነው”እንዲል፡፡ መዝ.፻፵፩÷፲፬፡፡፪ኛቆሮ፩÷፲፰፡፡የታማኙ እግዚአብሔር ተገዢ የሆነ ክርስያን በበኩሉ ታማኝ ይሆን ዘንድ ይገባዋል፡፡

እግዚአብሔር በታማኝነት የሚያመልኩትንና የሚያገለግሉትን ይፈልጋል፡፡በታማኝነት ጸንተው ለተገኙትም የበለጠ ዋጋን ይሰጣቸዋል፡፡ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርሰቶስ ይነግድበት ዘንድ ባለጠጋው አምስት፤ሁለትና አንድ መክሊት ስለተሰጣቸው ሰዎች በምሳሌ ባስተማረበት አንቀጽ ውስጥ በጥቂት ነገር ታማኝ መሆን የሚያሰጠውን ዋጋ አስተምሯል፡፡ማቴ.፳፭÷፲፬-፴ በምሳሌው እንደተጠቀሰው በጥቂት ገንዘብ ማለት በአምስና በሁለት መክሊት የታመኑ ሰዎች ታላቁን ክብር አግኝተው ወደ ጌታቸው ደስታ ገብተዋል፡፡እንደዚሁም ሁሉ በዚህ ዓለም ሲኖሩ ታማኝነት ገንዘብ ያደረጉ ሰዎች ታላቁን ዋጋ በማግኘት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባትን ያገኛሉ፡፡

የአንድ ክርስቲያን ታማኝነቱ የሚለካው በትንሹ ነገር ላይ ነው፡፡ በወንጌል እንደነገረው በጥቂቱ ፤በሰው(በሌላ) ገንዘብ ላይ ታማኝ የሆነ በብዙና በራሱ ገንዘብ ደግሞ ተማኝ ይሆናል፡፡

በአንድ ምዕመን ሕይወት ውስጥ ሊኖረው ስለሚችለው ታማኝነት መጠንም “እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን” ተብሏል፡፡ራእ.፪÷፲፡፡ራሱን እስከ መሠዋት መድረስ እንዳለበት ያሳያል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጵውሎስ የዕብራውያን ሰዎች ሓጢአትን ጸንተው ባለመቃወማቸው “…… ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም” በማለት የገሠጸው ተግሣፅ ምእመናን እስከ ምን ድረስ ታማኝ መሆን እንዳለባቸው ያሳያል፡፡ዕብ.፲፪÷፬፡፡

ታማኝነት በአንድ መልክ ብቻ የሚገልጽ ሳይሆን በአንድ ሰው መንፈሳዊውም ሆነ ሥጋዊ ሕይወት ውስጥ መገለጥ መኖር ያለበት ሥነ ምግባር ነው፡፡

## ሀ ታማኝነት ለእግዚአብሔር

እግዚአብሔር ራሱን ዝቅ አድርጎ የሰውን ሥጋ እስከመዋሐድ፤በሞቱና በትንሣኤው ሰውን ለዘላለም ሞት ለማዳን ሲል የገባውን ቃል ኪዳን በመፈጸም ታማኝነት ከሆነ ሰውስ ምን ያህል ለእግዚአብሔረ ታማኝ መሆን ይጠበቅበታል?

ሰው ለእግዚአብሔር ታማኝ ነው ማለት በማንኛውም ነገር እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ነገር አይፈጽምም ማለት ነው፡፡ቢፈጽምም በንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ ጊዜ አይፈጅም፡፡እግዘአብሔር በኃጢአቱ እስኪቆጣውም አይጠብቅም፡፡

ዮሴፍ “በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጠአትን እሠራለሁ ” ለማለት የበቃው ለእግዚአብሔር ታማኝ ስለነበረ ነው፡፡ዘፍ.፴፱÷፱፡፡ አንድ ሰው ኃጢአት ሲሠራ “በቅድሚያ የሚበድለው፤ የሚጋፋውና የሚዳፈረው እግዚአብሔርን ነው፡ምክያቱም ምሉዕ በኩልሔ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአትን የሚሠራው የልቦናውን ወቀሳ ጥሶ፤ሕገ እግዚአብሔርን ተላልፎ ሊያጸደቀው ሊኮንነው የሚችለው እግዚአብሔር እያየው መሆኑን ዘንግቶ አልያም ችላ ብሎት ነውና፡፡ ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት “አንተን ብቻ በደልሁ በፊትህም ክፉትን አደረግሁ” ሲል የምናገኘው ሰው ባደረገው ኃጢአት ከሁሉም በላይ የሚበድለው እግዚአብሔርን ስለሆነ ነው፡፡መዝ.፶÷፬፡፡ ምክንያቱም ኃጢአትን የሚያደርግ ሰው በሕገ እግዚአብሔር ላይ ዐምጸ ነውና፡፡

አንድ ክረስቲያን ለእግዚአብሔር ያለው ታማኝነት የሚገለጠው ኃጢአትን ባላመፈጸም ብቻ አይደለም፡፡ ነገር ግን እንደ ክረስቲያንነቱ ለእግዚአብሔር ብሎ ሊፈጽመው የሚገባውን ሁሉ በመፈጸም ጭምር ነው እንጂ፡፡ ስለሆነው ሁሉ እግዚአብሔርን ማመስገን፤በየለቱ ለተወሰኑ ሰዓታት ቃለ እግዚአብሔርን መማር፤ለዘላለም ሕይወት የተሰተውን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ንስሐ ገብቶ መቀበል፤በተሰጠን ጸጋና ጊዜ ቤተ እግዚአብሔርን ማገልገል፤ዓሥራት በኩራቱንና ቀዳምያቱን በትክክል ለቤተ ክርስቲያን መስጠት፤ በስዕለት የገቡትን ብፅዓት በአግባቡ መፈጸም ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ያለው ታማኝነትን የሚገለጥባቸው ናቸው፡፡

ክርስቲያን በታማኝነት በቁርጥ ኅሊና ስለ እግዚአብሔር ብሎ ሊሠራው የሚገባን ሁሉ በሚፈጽምበት ወቅት ከተለያዩ አቅጣጫዎች ፈተናዎች ሊያጋጥሙት ይችላሉ። በዚህ ወቅት እግዚአበሔር በሕግ በአምልኮ ወደ እርሱ ቀርበው በፍቅሩ የጸኑትንና በታማኝነት የሚያገለግሉትን በረድኤቱ ከመከራውሁሉ እንደሚያድናቸው ማመን ተገቢ ነው። እርሱ “ አልተውህም ከቶም አልጥልህም” ብሏልና። ሠለስቱ ደቂቅ ከእሳት የተጣሉት፤ ሐዋርያት “ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይገባል” በማለት ለባለሥልጣናቱ መልስ የሰጡት ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆነ ሰው በመከራውና በሞቱ እንኳን ታማኝነቱን መግለጥ ስላለበት ነው።

**ለ. ታማኝነት ለራስ**

ለራስ ታማኝ መሆን ማለት ሥጋዊውን ሆነ መንፈሳዊውን ሕይወት ከሚጎዳ ነገር ርቆ ወደ እውነተኛው ዓላማ ሊያደርስ የሚችለውን ዓላማና መንገድ መያዝ ማላት ነው።

“ለተራበች ነፍስ የመረረ ነገር ሁሉ ይጣፍጣል” እንደተባለ ነፍሱ ቃለ እግዚአብሔርን፤ ፍቅር እግዚአብሔርን ንስሐንና ሥጋ ወደሙን ተርባ ወደ መረረ ነገር ወደ ኃጢአት እንዳታዘነብል ተግቶ ይመግባታል።በዓይኑ ክፉውን ተመልክቶ፤ በአንደበቱ ዋዛ ፈዛዛውን ተናግሮ፤ በእጆቹ ክፉ ሠርቶ፤በእግሩ ወደ ማይገባ ቦታ ተራምዶ ሄዶ …… መከራ እንዳይመጣበት

ይጠነቀቃል።በሥጋዊውም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለትልቅ ደረጃ እንኳን ቢበቃ ለራሱ የሚታመን ሰው ተዘልሎ አይቀመጥም ።ያለውን ሳይሆን የሚቀረውን ያስባል። ራዕ.፫፥፲፪-፲፫። በዚህም የተነሣ ሕይወቱ (ክርስትናው) ዘወትር ዕድገት የሚያሳይ ይሆናል። በውኃ ዳር እንደተተከለች አትክልት ዘወትር ይለመልማል።ፍሬም ያፈራል።

ለራሰ ታማኝ የሆነ ሰው ከሥጋም ሆነ ከኅሊና አሊያም ከሌላ ቦታ የሚመነጩ ስሜቶችንና ምኞቶችን በምክንያት ደጋግሮ በልቦናው ተቀባይነት እንዲያገኙ ራሱን አያታልልም።ለሠራው ኃጢአትም ታምኖ ንስሐ ከመግባት በስተቀር ምክንያት በመደርደር ከንስሐ አይዘገይም፤ አይርቅምም።በልቦና የሚመላለሱት አዳዲስ ሐሳቦች ወደ ሕይወቱ ሠርጸው ሥር ከመስደዳቸው በፊት ያርቃቸዋል አሊያም ይሸሻቸዋል።ለራሱ ታማኝ የሆነ ሰው ያለ ሥራ የሚያሳልፋቸው ጊዜያት የሉትም። ሥራ ፈትቶ መቀመጥ የሥጋም የነፍስም ድህነትን የሚያመጣበት በመሆኑ በጊዜው ሁሉ ተግቶ ይሠራበታል።ዕረፍተ ሥጋን በመሻት ሥጋው በነፍሱ ላይ እንድትሰለጥን አይተዋትም።ይልቁንም ተግቶ ሰውነቱን በሥራ ይነስመዋል።

**ሐ. ለሌላው መታመን**

ታማኝ መሆን ለእግአብሔርና ለራስ ብቻ አይደለም።ለሌላውም ጭምር ነው እንጂ። ሌላው ሲባልም ሚስት ለባሏ ባል ለሚስቱ ፤ልጆች ለወላጆቻቸው ሠራተኛ ለአሠሪው፤ሕዝብ ለመንግስት፤ መንግሥትም ለሕዝብ የመሳሰለውን ነው።የዚህም መሠረቱ ባልጆራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ ያለው ነው።ማቴ.፳፪፥፴፱

አንድ መእመን እግዚአብሔርን በፍጹም ነፍሱ ከወደደ፤ ለእግዚአብሔርም በሁሉም ከታመነ ለሌላው( ለባልንጀራው) የግድ የታመነ ይሆና። ለባልንጀራው ታማኝ መሆኑንም በኅብረተሰቡ መካከል ባለው ሱታፌ ፤በሚያደርገው እንቅስቃሴ ይገልጠዋል።

በአነጋገሩ፤በአለባበሱ ፤በአኗኗሩ፤በሥራ አፈጻጸሙ፤በመሳሰሉት ታማኝነቱን ይገልጣል። ክርስቲያን ለሌላ ታማኝ ሲሆን አነጋገሩ የአድማጩን ኅሊና እንዳይጎዳ ወይም የተሳሳተ ግንዛቤ እንዳያስጨብጥ ያስባል። አለባበሱ እንዳያሰናክል፤ሥጋዊ ፍትውትን በሌሎች ላይ እንዳያመጣ ይጠነቀቃል። “ወንድሜ የሚሰናከል ከሆነ ለዘለዓለም ሥጋ አልበላም ” ፩ኛቆሮ.፲፥፲፫ የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል መመሪያው ያደርጋል።በሥራ ቦታው የሥራ ሰዓት በማክበር፤በሥራ ሰዓት የሚጠበቅበትን ሥራ ያለልግመት በመፈጸም፤ ለመሥሪያ ቤቱ ንብረቱና ገንዘብ ጥንቃቄ በማድረግ ታማኝነቱን ይገልጣል።

በአንድ ጊዜ ታማኝ መሆን ሊከብድ ይችላል። ይሁን እንጂ ከአቅሙ በላይ በሆነው ደግሞ እንዲታመን እግዚአብሔር ኃይሉን ይሰጠዋል።አንድ ክርስቲያን፦

በጥቂቱ ነገር ታማኝ ከሆነ እግዚአብሔር በብዙው እንዲታመን ያደርገዋል።

በቤቱ ለሁሉ ከታመነ እግዚአብሔር ደግሞ በቤተ ክርስቲያን በአደባባይ እንዲታመን ያደርገዋል።

ለራሱ ነፍስ ከታመነ ለወገኑ ሕይወት እንዲታመን ያበረታዋል።ቅዱስ እስጢፋኖስ የተጠራው በማዕድ ሥራ ሲያገለግል ነበር።ይህንንም ሥራውን በንጽሕና በታማኝነት ስለሠራው እግዚአብሔር አይሁድ ሊከራከሩት እስኪሳናቸው ድረስ የሚያስተምር ሐዋርያ አደረገው።ሰማያዊውን ምሥጢር ለማየትም አበቃው።የሐዋ.ሥራ.፮-፯

በአጠቃላይ ታማኝነት አንድ ምእመን የእግዚአብሔር ገንዘብ መሆኑ የሚለጥበት፤ክፉውን መጠየፉ የሚታወቅበት ምግባር ነው።ስለሆነም ክርስትያን ሁሉ ይህቺን መልካምና ወደ ምንግሥተ ሰማያት ለመግባት የምታስችለውን ምግባር ለመያዝ መትጋት አለበት። በተሰማራንበት አገልግሎት ሁሉ የታመንን ሆነን እንድንገኝ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት የእግዚአብሔር ቸርነት ከእኛ ጋር ይሁን።

“ክርስትያናዊ ስነ ምግባር“

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን